# እኔ የነጻነት መንፈስ ነኝ፤የመለስ ዜናዊ መርዘን

ይህ አስተያየት የሚያተኩረው በቅርቡ አዳል ኢሳው በሚል መጠሪያ “የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴ” መስሪያቤት በአይጋ ፎረም ድህረ ገጽ ላይ ያወጣውን ጽሁፍ በተመለከተ ነው።ይኸው ጽሁፍ የግንቦት 7 መሪ ብርሀኑ ነጋ በግዳጅ ተይዘው ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ በመጠየቅ ላይ ያነጣጠረ ነው።እንደጽሁፉ አባባል እሱ ”አሸባሪ” ነው።ስለ አሸባሪነት ሕጋዊ ትርጉም መነጋገሩን እዚህ ላይ እንለፈውና ምን አይነት ሕጋዊ መንግስት ነው በሚለው ጉዳይ ላይ ማጠንጠኑን ልምረጥ፤ጽሁፉ የአገዛዙ መሪ ቀጥተኛ ሀሳብ መሆኑን ነጋሪ የሚሻው ጉዳይ አይደለም።

በእርግጥም ከዚህ የበለጠ እንድንጠብቅ የሚያደርገን ነገርም የለም። ከዚህ አገዛዝ የሚጠበቀው ይኸው ነው ።ሆኖም አሁንም አንድ ነገር ማስቀመጥ ግን ያስፈልጋል።ከነሱ አመለካከት እንኳን ብንነሳ የሚማስኑት ለተኮላሸ ነገር ነው።

ይህ ጽሁፍ በትክክልም የአገዛዙ መስታዊት ነው።የሚነግረን ለኢትዮጵያዊያን ዜጎች ሀላፊነት የሌለበት እና የገዥውን ፓርቲ ባህሪ የሚያመለክትና የእርሱን ጥቅም ገቢራዊ ለማድረግ እንደተነሳ የሚገልጽ ነው። ድርጊቱም መሰረታዊን የነጻነትና ዴሞክራሲን ትግል የሚያፍን ተግባር ነው።

ከሁሉም በላይ ዋናው ትኩረቱ የዶክተር ብርሀኑ በግዳጅ ወደ ሀገር ቤት መመለስን የተመለከተና አሜሪካም እንድትታደገው የቀረበ ተማጽኖ ነው።ከመልሱልኝ ጥያቄ አልፎም ለደብዳቤው ተገቢውን ምላሽ አሜሪካ ካልሰጠች በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው “የፀረ-ሽብርተኝነት” ውል አደጋ ላይ ለወድቅ እንደሚችልም ለማስጠንቀቅ ይከጅለዋል።

ጽሁፉ በጀርባ አጥንትነት የያዘው መልክት ደግሞ ሀገሪቱ ”ከአለም ሀገራት ሁሉ እጅግ በጣም የከፋ ጎረቤት ሀገር አዋሳኝ ያላት” መሆኑንም ያሰምርበታል።ይህም በምርጫ ሳይሆን ያለነገር ነው ሲል ይደመድመዋል።አገዛዙ ይህንን ክልል እንደ ማይወደው ለማሳየትም የተጠቀመበት አባባል አለው። ከሁሉ በላይ በዚህ “የከፋ ጎረቤት ሀገር” በሚለው በጸረ-ሽብርተኝነት ስ
ይኸው አገዛዝ ነው።

ይህም በመሆኑ ነው።እራሱን  በአሜሪካ ተወዶ እንዲቆይ ያደረገው።አገዛዙ ገና ከጨቅላነቱ ጀምሮ የአሜሪካ ጥቅም ጠባቂ ነው። በማንኛውም ሁኔታ “የኢትዮጵያን” ጥቅም ሲገልጽ አልታየም።  በሕዝብ ተመራጭ ሆኖ እውቅና ያገኘ መንግስት ባለመሆኑ ኢትዮጵያን ለምን እውቅና አልሰጠህም ብሎ የሚጠይቅ የለም። በተለይ ከ1997 ምርጫ በኋላ በግልጽ የወጣ የአደባባይ ሚስጢር ነው። አገዛዙ አሁን ደግሞ ያመጣው ሀሳብ ”የልማት መንግስት” በሚል እራሱን ህልውና ትክክለኛ ለማስመሰል ያጸለቋቁሳል። ነገር ግን በዚህ ጽሁፍ ይኸው የማስመሰያ ልማት እንኳን አልተጠቀሰም። ምን አልባትም የትም ሊያደርሳቸው ያለማቻሉን አውቀውት ይሆናል።

እነዚህን ሁሉ እናስብና፤የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ አሜሪካ እንድትታደገው ቀጥተኛ ጥራቄ ማቅረቡ ምን አልባት አግባብ ሊሆን ይችላል።ከሁሉ በላይ ግን እንደ አገዛዙ መግለጫ የአሁኑ ተቃውሞ ከወታደሩ ወገን መሆኑ ነው። ወታደሩን በሀሳብ የማይስማሙትን ለማፈንና ጭቆናውን ለማስፈጸም እንዴት እንደ ተጠቀመባቸውና ለወደፊቱም የነበረውን የጸና እምነት አስቡት።አሁን ጉዳዩ ወደ

ወታደሩ መሸጋገሩ የአገዛዙ መሰረት መናዱን የሚያመለክት ነው።ባለፋት በርካታ አመታት በወታደሩ ወስጥ በፖለቲካ ላይ መሰረት ያደረገ ከስራ መፈናቀል አድርጓል።ለመሰናበታቸውም ምክንያት የሰጠው የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን ይደግፋሉ የሚል ነው። በወታደሩ ውስጥ የከፍተኛው ወታደራዊ እዝ ቦታወች በአገዛዙ ታማኞችና የብሄረሰብ አባላት የተያዙ ናቸው ።ይህ ሁሉ “ቅድሚያ ጥንቃቄ” ቢደረግም ወታደሮች ይህንን አገዛዝ  በግልጽ ወደመቃወም ደረጃ ተሸጋግረዋል። ስለሆንም በሕዝቡ የማይደገፍ አገዛዝ  የእርሱን ሕጋዊነት ለማሳየት መሞከር ውጤቱ እየመከነ መጥቷል። የራሱ ወታደር የተቃወመውና ሕዝብ አንቅሮ የተፋው አገዛዝ አንድ ወገን እርዳታ መጠየቅ አለበት ይኸውም የውጭ ሀገር እንዲታደገው መማጸን ነው።

ዶ/ር ብርሀኑ ሕገ ወጡን አገዛዝ እየታገሉ ባሉበት ውቅት የብርሀኑን ስም መከላከያ ሚኒስቴር እንዲይዘውና ወደ ሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያስተላልፍ መጠየቅ አሜሪካ ሕግና ደንብ እንደሌለ አይነት መቁጠር ነው። ብርሀኑ ነጋ እንዲመሰሉ መጠየቁ እራሱ በአሜሪካ አስተዳደር አትርሱኝ ከሚል መልክት ውጭ ሌላ የሚፈይደው ነገር የለም።

አወ የተለያዩ የአሜሪካ መንግስት ድርጅቶች ሰውን ሽበርተኛ ነው ሊሉ ይችላሉ። ምክንያቱም አንዳድ መንግስታት ልምድ ስለሆነባቸው ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ ሽብርተኛ ብለው ስም ስለሚሰጡ፣ እነሱ ይህንኑ የስም ልጠፋ ሊጠቀሙበት ይችሉ ይሆናል። አሜሪካ የሰብአዊ መብት መርህ መሰረት የተጣለበት ሀገር ነው። የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን አሜሪካ የተመሰረተችበትን ባህሪ ካለመረዳት የመነጨ አቀራረብ ነው። መግለጫው የሚያረጋግጠው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ውስጥ  እንዴት ሥራ እንደሚሰራ የሚያስረዳ ነው።በዚህ ሂደት የኢትዮጵያ ዳኞች እና ሌሎች የመንግስት ተቋማት በተደጋጋሚ ያረጋገጡት ነገር እራሳቸው የግዥው ፓርቲ ጭቆና እና ግፍ አስፈጻሚ መሆናቸውን ነው።

የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚንስቴር አንዳስረዳው የብርሀኑ ነጋ ወደ ኢትዮጵያ ተገዶ መመለስ “ የኢትዮጵያን ፀረ-ሽብር” ተግባር “ውጤታማ” ያደርገዋል። ይህ ማለት አገዛዙ ለዴሞክራሲና ለፍትህ የሚደረገውን ትግል ማዘግየት ወይም ማጥፋት ተልኮው አድርጎ እየሰራ ያለ መሆኑን ነው። ይህንን ቀደም ብለን እናውቀዋለን፤ ለምን ቢሉ ይህ ባለፈው 18 አመታት ስንሰማው የቆየ ትረካ ነው። ይህ ግለሰቦችን እየተከታተሉ ማጥቃት የአገዛዙ ገላጭ ባህሪም ነው።

እስኪ ለውይይት ያህል አንድ ነገር እንገምት፤ የአሜሪካ መንግስት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ አደረገ እንበል፤ በተደጋጋሚ ወደ ነበረበት እስር ቤትም ገባ፤ወይም ምን አልባትም ተገደለ ።ይህ ውጤት ያመጣል? በፍጹም ውጤት የለሽ ነው። የገዛዙ አንዱ ችግሩ የዲሞክራሲና የፍትህ ጥያቄ የሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ መሆኑን ካለመረዳት የመነጨ ነው።ይህ ባይሆን ኑሮ በመጀመሪያ የስልጣን መቆናጠጫ ዘመናቸው በህገ ወጥ ተቃዋሚነት ፈርጀው የገደሉት ኦሮሞ ወጣት ግድያ በኋላ ሁሉ ነገር በቆመ ነበር። ይህ ባለመሆኑ ግን ቁጥራቸው የትየ ሌሌ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ባመኑበት ሕይወት ውስጥ ቀጠሉ። ይህ አንድ ብለን ብዙ ብዙ ቆጥረን እንሸጋግርና ከወራት በፊት ብርቱካን ሚዴቅሳን ለህገወጥ እስርቤት ሲዳርጉም ይኸው የፍትህና የዴሞክራሲ ጥያቄ በቆመ ነበር።

ዶ/ር ብርሀኑ የትግል ወንድማችን ነው። ልክ እንደሁላችንም ነው። መስዋእትነትን ተረድቶ የጨቋኙን አገዛዝ ለመታገል ያወጀ ነው። መታሰር ወይም አለመታሰር፤ መሞት ወይም በሕይወት መኖር ፤በግዳጅ መመለስ ወይም በስደት መኖር፤ ኖሩ አልኖሩ ሕወሀትን መታገሉ ቀጣይ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ይህንን ህገወጥና ጨቋኝ መንግስት ማስወገዳችን አይቀሬ ነው።

አገዛዙ ማወቅ የሚገባው ነገር ቢኖር ግለሰቦችን መግደልና ማሰር የሚችቹን እምነት አይቀንሰውም። ይበልጥ የሚያድግበት ወቅትና በሚሊዮን ወደ ሚቆጠሩ የእምነቱ ተከታወች ይሸጋገራል።ከጥቂት ሳምንታት በፊት የአገዛዙ አፈቀላጤ ብርሀኑ ነጋ በውጭ ተቀምጦ እንዴት መንግስትን ለመገልበጥ እንደሚሰራ ሲጠይቅ ነበር። “እሱ በአሸጋግሮ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ሊጠቀም ነው?” በማለት ለማሽሚጠጥ ሞከረ።ግን ብርሀኑ አገር ቤት ከሚኖሩ በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር በእምነት የተቆራኘ መሆኑን አለመረዳት ነው ለዚህ ትችት የዳረገው።በዚህ ሳምንት ደግሞ በሀገር ቤት በስራ ላይ በሚገኙ ጀነራል መኮንኖች የተሞከረውን ፈንቅለ ወያኔ መንግስት ዋናው አቀነባባሪ ብርሀኑ ነጋ ነው በማለት ይከሳሉ።እንድግዲህ የእርስ በእርሳቸውን መቃረን በይበልጥ ተመልከቱ። በነገራችን ላይ ግንቦት 7 ይህንን ክስ አስተባብሏል።

አቤቱታው ከአገዛዙ ከራሱ እስከመጣ ድረስ እና እንደምክንያት ከተቆጠረ ምንድን ነው ይኽ ለእነርሱ የሚያስተምረተው? ብርሀኑ ነጋ ሰዎችን እንደዚህ አይነት በሕይወታቸው ላይ አደገኛ እርምጃ ውስጥ እንዲገቡ በአሸጋግሮ መቆጣጠሪያ መሳሪያ አልተጠቀመም። እነዚህ አመዛዝነው መርጠውና መጥነው መራመድ የሚችሉ አዋቂና በእራሳቸው ውሳኔ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ናቸው። በግልጽ ይህ የሚያሳየው እነዚህ ሰዎች ገዥው ፓርቲ እንደሚያወዛውዛቸው እንደመጀመሪያዎቹ ተሳቢ ጀነራሎች/እንደ ጀነራል ካሳ ደሜ አይነቶች/አይደሉም። እነዚህ ሰዎች በራሳቸው የሚያስቡ ብቁ ሕሊና ያላቸው የከፋ አደጋ የተደቀነባቸው መሆኑን ቢያውቁም የመረጡትን ለማድረግ የወሰኑ ናቸው።በቂ ምክንያትም ኣላቸው፤ አስበው ማደረግ ያለባቸውን አድርጋዋል። እንደነሱ የሚይያስቡ ብዙ ሰዎች በወታደሩ ውስጥ እና በየትም ቦታ አሉ። ይህ ከሆነ ግለሰቦችን በማጥቃት ሕዝባዊ ሰደዱን ሊያጠፉት አይችሉም።

መልሱ አጭርና ግልጽ ነው።መሪዎችና ጋጠወጦች የግለሰቦችን ምርጫና መርህ አያውቁም።ይህ የራሱ ማስረጃ ሊሆን ይገባል። ይህን ማድረግ ቢችሉ ኑሮ አምባገነን ባልሆኑ ነበር። ሰዎችን በገንዘብና በጥቅማትቅም መሽምገል ደረጃ ያዘቀዘቁበት፤ የመወረዱበትና በራቸውን ለብኩንነት ወለል አርገው የከፈቱበት ሁኔታ በፍጹም አያውቁትም፡ ገምቱ ከሁሉም ነገር ነጻ ናቸው? ይህ ሁሉ አንድን ነገር ለማስፈጸም እርሷ /እሱ “አምነውበት ነው?”

ካለፈ ሁኔታ ለመማር የተዘጋጁም አይደሉም። በተደጋጋሚ ጊዜ ብርሀኑን አሰሩት ሲፋታ ግን ይበልጥ ጠንካራ እየሆነ ሄደ እንጂ ቅስሙ አልተሰበረም። በእነርሱ አስተሳሰብ ቅንጅትን ማጥቃታቸው የዴሞክራሲ ሂደቱን ያስቆሙ መሰላቸው፤ ግን ማንነታቸውን በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ፊት እርቃናቸውን መቆማቸውን ነው ያረጋገጡት። በተቃራኒው ትግሉም ይበልጥ ውስብስብ እየሆነ ወደ እነርሱ እየመጣባቸው ነው።

የፍትህና የዴሞክራሲ ትግል ከእለት እለት እየጨመረ፤ እየጎለበት በመሄድ ላይ ነው። ድርጅቱ ምንም አይደል የእኛ እምነት ነጸብራቅ ነው።በማንኛውም ወቅትና ጊዜ መሪዎቹ ሲጠቁ ብዙዎቻችን ፍትህ አለመኖሩን በበለጠ እየነቃን

እንድንመጣ ያደርገናል።ጥቃቱ በከፋ ቁጥር ብዙ እንድንቀራረብ ያደርገናል። በጋራም ለፍትህ መኖርና የመጠየቅ እድላችን ያሰፋዋል።

ግንቦት 7ን ማንም ሊያግደው አይችልም።ምክንያቱም እኔ ግንቦት 7 ነኝ። እናም እኔ አለሁ ከበፊቱ ነጻ ነኝ .በአዲስ አበባ ስታስረኝ በጋምቤላ ነጻ እሆናለሁ፤በጎንደር ስትገለኝ በወለጋ በህይወት እገኛለሁ፤ በአዳማ ስታሳድደኝ በወልቃይት ጠገዴ ወጣቶች ጆሮ ውስት የነጻነትን ዋሽንት እየነፋሁ አለሁ። ይህ ደወል ነው በውድቅት ሌሊት መርዘን/የራስ ምታት/ የሚሆንብህ። እህቴን ልትደፍራትና መንደራችን በኦጋዴን ልታቃጥለው ትችል ይሆናል። ነገር ግን በትግራይ ደረሰ በማለት ስታማርር የነበረውን ሰቆቃ እየተመገብኩ መሆኔን ግን አትርሳ። በወላይታ በቀን የሸማ ሥራ  እሰራለሁ፤በምሽት በአራዳ የቡና ቤት ሰራተኛ ነኝ፤ በርካታ ቋንቋወችን እናገራለሁ፤ መልክቴ እንዲደርስህ ልኬብህለሁና አደራህን በቀጣዩ ስብሰባህ ተነጋገርበት። አሸንፍሀለሁ!! እኔ ግንቦት 7 ነኝ፡ ለአንድነት፤ለፍትህ እና ለነጻነት ቆሜአለሁ።በማንኛውም ቦታና ስፍራ እገኛለሁ።